የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር

# AFRICAN CHARTER ON THE RIGHTS AND WELFARE OF THE CHILD

## መግቢያ

የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር በሚል ርዕስ የተሰየመውን ይህንን ቻርተር የተቀበሉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት፤

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ለሰብአዊ መብቶች አስፈላጊነት ዕውቅና መስጠቱን እንደዚሁም የአፍሪካ የሕዝቦችና የሰዎች ሰብአዊ መብቶች ቻርተር ማንኛውም ሰው የዘር፣ የጐሣ፣ የቀለም፣ የጾታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ፣ የዜግነት፣ የሀብት፣ የውልደት፣ የሌላ ደረጃ (አቋም)ን የመሳሰሉ ልዩነቶች ሳይደረጉ በቻርተሩ ዕውቅና ያገኙና የተረጋገጡ መብቶችና ነጻነቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደንገጉና ተቀባይነት ማግኘቱን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሀገራትና የመንግሥታት የመሪዎች ጉባኤ እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 17 - 20 ቀን 1979 ሞኖሮቪያ ላይቤሪያ ባካሄደው አሥራ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ የተቀበለው የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደኅንነት መግለጫ (ኤ.ኤች.ጂ/ኤስ.ቲ.4 አር.ኢ.ቪ.1) የአፍሪካን ሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ለማሳደግ (ለማጐልበት) እና ለመጠበቅ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች የመውሰድ አስፈላጊነትን በተመለከተ ያሳለፈውን ውሳኔ በማስታወስ፤

አብዛኞቹ የአፍሪካ ሕፃናት የሚገኙበት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ልማዳዊና የልማት ሁኔታዎች እንዲሁም በገጠማቸው የተፈጥሮ አደጋ፣ ወታደራዊ ግጭት፣ ብዝበዛ እና ረሃብ የተነሳ የሚገኙበት ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ መገኘቱን እንዲሁም ሕፃናት በአካልና በአእምሮ ያልጐለመሱ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማስተዋል፤

ሕፃናት በአፍሪካ ሕብረተሰብ ውስጥ ልዩና የላቀ ቦታ ያላቸው መሆኑና የተሟላና የተስተካከለ ስብእና ይዘው እንዲያድጉ ፍቅር፣ ደስታ እና መግባባት ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ማደግ እንዳለባቸው በመገንዘብ፤

ሕፃናት በአካልና በአእምሮ ያልጐለመሱ በመሆናቸው ምክንያት ጤንነታቸውን፣ አካላቸውን፣ አእምሯቸውን እንዲሁም የግብረ-ገብ እና ማኅበራዊ እድገታቸውን በተመለከተ ልዩ እንክብካቤ

የሚሹና እንደዚሁም ክብራቸውን፣ ደኅንነታቸውን እና ነጻነታቸውን መሰረት ያደረገ የሕግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የሕፃናት መብቶችና ደኅንነትን ፅንሰ ሃሳብ የሚያዳብሩና በምሳሌነት የሚወሰዱ የአፍሪካ ባህል፣ ታሪክ እና የሥልጣኔ እሴቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

የሕፃናት መብቶችንና ደኅንነትን ማራመድና ጥበቃ ማድረግ እያንዳንዱ ሰው የበኩሉን ድርሻ እንደተወጣ የሚያመለክት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

በአፍሪካ አንድነት ድርጅት እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በወጡ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት መግለጫዎች፣ ስምምነቶች እና ሌሎች ሰነዶች ውስጥ የተመለከቱ በተለይም በተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ በአ.አ.ድ. የሀገራት እና የመንግሥታት መሪዎች የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት መግለጫ ውስጥ የተደነገጉ መርሆዎችን ለማስፈጸም ቃል መግባታቸውን በድጋሚ በማረጋገጥ፤

እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

## ክፍል 1

## መብቶችና ግዴታዎች

## ምዕራፍ አንድ፣ የሕፃናቶች መብቶችና ግዴታዎች

### አንቀጽ 1

### የተዋዋይ ሀገራት ግዴታ

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የሆኑ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት በቻርተሩ ለተደነገጉ መብቶች፣ ነጻነቶችና ግዴታዎች ዕውቅና የመስጠት የቻርተሩ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ በቻርተሩና በየሕገ-መንግሥቶቻቸው በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሕግ ማውጣትን እና ሌሎች እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በዚህ ቻርተር የተደነገገው ቢኖርም ለሕፃናት መብቶችና ደኅንነት የላቀ (የተሻለ) ጥበቃ የሚያደርጉ የተዋዋይ ሀገራት ባወጧቸው ሕጎች ወይም በእነዚህ ሀገራት ተፈጻሚነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎች የተጠበቁ ናቸው፡፡
3. በቻርተሩ ውስጥ የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎችን የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ፣ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ድርጊት ቻርተሩን የተቃረነውን ያህል (በተቃረነበት ልክ) ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

ለዚህ ቻርተር አፈጻጸም ሕፃን ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

### አንቀጽ 3

### ልዩነት/መድልዎ ስላለማድረግ

ማንኛውም ሕፃን የወላጁ ወይም የአሳዳሪው ወይም የራሱ የዘር፣ የጐሳ፣ የቀለም፣ የጾታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ የዜግነት፣ የማኅበራዊ አመጣጥ፣ የሀብት፣ የውልደት ወይም በሌላ ዓይነት የመጣ ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ ቻርተር ዕውቅና በተሰጣቸውና በተረጋገጡ መብቶችና ነጻነቶች የመጠቀም መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 4
## የሕፃናትን ደኅንነት (ጥቅም) ስለማስቀደም

1. በመንግሥት ወይም በማንኛውም ሰው የሚከናወን ሕፃናትን የሚመለከት ሥራ ለሕፃናቱ ደኅንነት (ጥቅም) ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሃሳቡን ለሌላው ሰው ለመግለጽ የሚችል ሕፃን ጉዳዩ በሚታይበት በማንኛውም የዳኝነት ወይም የአስተዳደር አካል ላይ ሃሳቡን በቀጥታ ወይም ገለልተኛ በሆነ ወኪል አማካኝነት የሚያሰማበት ዕድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ የሚመለከተው አካልም ሕፃኑ የሰጠውን ሃሳብ በሕግ በተደነገገው መሰረት ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

## አንቀጽ 5
## በሕይወት መኖርና እድገት

1. ማንኛውም ሕፃን በተፈጥሮ ያገኘው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ይህ መብት የሕግ ጥበቃ ያገኛል፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የሕፃናትን ቀጣይ ህልውና፣ ጥበቃና እድገት በተቻላቸው መጠን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. በሕፃናት ለተፈጸሙ ወንጀሎች የሞት ቅጣት አይጣልም፡፡

## አንቀጽ 6
## ስምና ዜግነት

1. ማንኛውም ሕፃን ሲወለድ ስም የማግኘት መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሕፃን ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ የመመዝገብ መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም ሕፃን ዜግነት የማግኘት መብት አለው፡፡
4. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት አንድ ሕፃን ሲወለድ በሌላ ማናቸውም መንግሥት ሕጉን ተከትሎ ዜግነት ያልተሰጠው ከሆነ የተወለደበትን ግዛት የሚያስተዳድረው መንግሥት ዜግነት እንዲያገኝ የሚያስችሉ መርሆዎችን በሕገ-መንግሥትና በሌሎች ሕጎች ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 7
## ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት

በሕግ የተደነገጉት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሃሳቡን ለሌላው ማስተላለፍ የሚችል ሕፃን በማንኛውም ጉዳይ ላይ ያለውን ሃሳብ በነጻ የመግለጽ እና አስተያየቱን የማሠራጨት መብት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 8

## በማኅበር የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሕፃን በሕግ መሠረት በነጻ የመደራጀት እና በሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብ መብት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 9

## የአመለካከት፣ የኅሊና እና የሃይማኖት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን በነጻነት የማሰብ፣ የኅሊናና የሃይማኖት መብት አለው፡፡
2. ሕፃኑ በእነዚህ መብቶች ሲጠቀም ወላጆቹ ተቀባይነት ባገኘ ጊዜም ሕጋዊ አሳዳሪዎቹ የሕፃኑን ደኅንነት (የተሻለ ጥቅም) ወይም በመታየት ላይ ያለ ችሎታውን ግምት ውስጥ ያስገባ አቅጣጫን ማመልከትና መመሪያ መስጠት አለባቸው፡፡
3. ብሔራዊ ሕጐችና ፖሊሲዎች እንደተጠበቁ ሆነው መንግሥታት የሕፃኑ ወላጆች፣ ተቀባይነት ባገኘ ጊዜም ሕጋዊ አሳዳሪዎች በእነዚህ መብቶች አተገባበር ላይ ለሕፃናቱ መመሪያ የመስጠት ወይም አቅጣጫን የማሳየት ግዴታቸውን ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 10

## የግል ሕይወት የተጠበቀ ስለመሆኑ

ወላጆች ወይም ሕጋዊ አሳዳሪዎች ጠባዩን በተመለከተ በሕፃኑ ላይ ተመጣጣኝ ቁጥጥር ለማድረግ ያላቸው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሕፃን በግል ሕይወቱ፣ በቤተሰቡ ቤት ወይም በግል ግንኙነቱ ውስጥ ከሚደረጉ ሕገ-ወጥ ጣልቃ ገብነቶች ወይም በክብሩና መልካም ዝናው ላይ ከሚሰነዘሩ ጥቃቶች የመጠበቅ መብት አለው፡፡ ሕፃኑ ከእነዚህ ጣልቃ ገብነቶችና ጥቃቶች እንዲጠበቅ ሕጋዊ ከለላ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 11

## ትምህርት

1. ማንኛውም ሕፃን የትምህርት መብት አለው፡፡
2. ለሕፃኑ የሚሰጠው ትምህርት፤

   ሀ/ በተፈጥሮ ያገኘውን ስብእና፣ ተሰጥኦ እንዲሁም አእምሯዊና አካላዊ ችሎታውን በማሳደግና በማጐልበት፤

ለ/ በተለይም በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ሰነዶች እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫዎችና ስምምነቶች ላይ የተመለከቱ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች እንዲተገበሩ በማድረግ፤

ሐ/ ተቀባይነት ያላቸው የአፍሪካ ግብረ-ገቦች፣ ልማዳዊ እሴቶች እና ባህሎች በመጠበቅና በማጠናከር፤

መ/ ሕፃናቱ በማናቸውም ሕብረተሰብ ውስጥ ዘር፣ ጐሳ ወይም ሃይማኖት ሳይገድባቸው በመግባባት፣ በመቻቻል፣ በመነጋገር፣ በመከባበርና በወዳጅነት መንፈስ ላይ የተንተራሰ የኃላፊነት ስሜት እንዲኖራቸው በማዘጋጀት፤

ሠ/ የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ነጻነትን በመጠበቅ፤

ረ/ የአፍሪካ አንድነትና ውኅደት በማራመድ እና በማሳካት፤

ሰ/ ለተፈጥሮ ሀብቶችና ለአካባቢ ያለውን ክበሬታ በማሳደግ፤

ሸ/ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አጠባበቅ ላይ ሕፃኑ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት፡፡

3. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ይህ መብት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እንዲሆን ማንኛውንም አግባብነት ያለው እርምጃ መውሰድ ያለባቸው ሲሆን በተለይም፡-

ሀ/ ነጻና አስገዳጅ መሰረታዊ ትምህርት የመስጠት፤

ለ/ በተለያየ ደረጃ የሚሰጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲጐለብት/እንዲስፋፋ በማበረታታት ለሁሉም በሂደት እንዲዳረስ የማድረግ፤

ሐ/ በችሎታና በአቅም ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ትምህርትን ለሁሉም እንዲደርስ የማድረግ፤

መ/ ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎችን ቁጥር እንዲቀንስ እና ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተገቢ ሁኔታ እንዲከታተሉ የሚያበረታታ እርምጃ የመውሰድ፤

ሠ/ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ሴቶች፣ ልዩ ተፈጥሮ ያላቸው እና ተጠቃሚ ሳይሆኑ የቆዩ ሕፃናት እኩል የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

4. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ወላጆች ተፈጻሚነት ባገኘ ጊዜም ሕጋዊ አሳዳሪዎች ለሕፃኑ የሚሰጠው ሃይማኖታዊና ግብረ-ገባዊ ትምህርት እየታየ ካለው ችሎታ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መሰጠቱን ለማረጋገጥ እንዲችሉ መንግሥት ካቋቋማቸው ውጪ ያሉ በመንግሥት የጸደቀውን ዝቅተኛ መመዘኛ የሚያሟሉ ሕፃኑ የሚማርባቸውን ትምህርት ቤቶች ለመምረጥ ያላቸውን መብትና ግዴታ ማክበር አለባቸው፡፡

5. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በትምህርት ቤት ወይም በወላጅ የዲሲፕሊን ቅጣት የተጣለበት ሕፃን በዚህ ቻርተር በተመለከተው ሁኔታ በሰብአዊነት ወይም ክብሩን በጠበቀ አኳኋን መያዙን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡
6. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ የፀነሱ ሕፃናት በየግል ችሎታቸው መሰረት ትምህርታቸውን የሚቀጥሉበት ዕድል መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡
7. ትምህርት ቤት የሚያቋቁሙና የሚያስተዳድሩ ተቋማት ወይም ግለሰቦች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተውን መርሕ መተግበርና በተቋማቱ የሚሰጠው ትምህርት በመንግሥት የሚወጡ መመዘኛዎችን የሚሟላት ግዴታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በነጻነታቸው ውስጥ ጣልቃ መግባትን በሚፈቅድ ሁኔታ አይተረጎምም፡፡

## አንቀጽ 12

## ዕረፍት፣ መዝናኛና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት ዕረፍት የማግኘት፣ የመዝናናት፣ ዕድሜያቸው በሚፈቅደው ጨዋታዎች የመጫወትና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች የማድረግ እንዲሁም በባህላዊና ሥነ-ጥበባዊ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ መብታቸውን ዕውቅና መስጠት አለባቸው፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት በባህላዊና ሥነ-ጥበባዊ ሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ ያላቸውን መብት የማክበርና መብቶቹን የማጎልበት፤ እንዲሁም ሕፃናቱ በባህላዊ፣ ሥነ-ጥበባዊ፣ የመዝናኛና የዕረፍት እንቅስቃሴዎች ላይ እኩልና ሚዛናዊ ዕድል እንዲሰጣቸው ማበረታታት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 13

## ስለ አካል ጉዳተኞች ሕፃናት

1. ማንኛውም አእምሮው ወይም አካሉ የተጎዳ ሕፃን ከመንፈሳዊና ከአካላዊ ፍላጎቱ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም ክብሩን የሚያረጋግጥ፣ በራስ መተማመኑንና በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ የሚያሳድግ የተለየ የጥበቃ እርምጃ ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የኢኮኖሚ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናትና እነርሱን ለመንከባከብ ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች ተስማሚና ሊተገበር የሚችል

ድጋፍ የማድረግ በተለይም ሕፃናቱ የተሟላ ማኅበራዊ ውኅደት፣ ግለሰባዊ፣ ባህላዊና ግብረ-ገባዊ እድገት እንዲኖራቸው በሚያስችላቸው አኳኋን የሥልጠና፣ የቅጥርና የመዝናናት ዕድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

3. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የአካልና የአእምሮ ጉዳተኛ ሰዎች በሕንጻዎች፣ አደባባዮች፣ ጐዳናዎች ወይም ለአካል ጉዳተኞች በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የያዙትን ዓላማ በሂደት ለማሳካት አስፈላጊውን ሀብት ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 14

## ጤናና የጤና አገልግሎት

1. እያንዳንዱ ሕፃን የላቀ የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ ጤንነት የማግኘት መብት አለው፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ይህን መብት በተሟላ ሁኔታ መፈጸም በተለይም የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

   ሀ/ የሕፃናትን ሞት መቀነስ፤

   ለ/ ለመጀመሪያ ደረጃ ጤና አጠባበቅ መስፋፋት የበለጠ ትኩረት በመስጠት ሕፃናት አስፈላጊውን የሕክምና እርዳታና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

   ሐ/ በቂ የተመጣጠነ ምግብና ንጽሕ የመጠጥ ውሃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

   መ/ በመጀመሪያ ደረጃ ጤና አጠባበቅ መዋቅር ውስጥ ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በሽታንና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን መከላከል፤

   ሠ/ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች ተገቢውን ሕክምና ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

   ረ/ በሽታን የመከላከል ዘዴዎች፣ ቤተሰባዊ ኑሮን የሚመለከቱ ትምህርቶች እና አገልግሎት አሰጣጥን ማስፋፋት፤

   ሰ/ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት መርሃ-ግብርን የብሔራዊ የልማት ዕቅድ አካል ማድረግ፤

   ሸ/ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ወላጆች፣ ሕፃናት፣ የማኅበረሰብ መሪዎች (የሀገር ሽማግሌዎች)፣ ሕብረተሰቡን የሚያገለግሉ ሠራተኞች ስለ ሕፃናት እንክብካቤ እና ስለተመጣጠነ ምግብ ያላቸውን መሰረታዊ ዕውቀት ሥራ ላይ ስለሚያውሉበት፣ ጡት ማጥባት ስላለው ጥቅም፣ ስለ አካባቢ ጤና አጠባበቅ እና በቤት ውስጥ የሚከሰቱ ሌሎች አደጋዎችን መከላከል ስለሚቻልበት ሁኔታ በቂ መረጃና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

ቀ/ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (ለትርፍ ያልቆሙ ማኅበራት) አካባቢያዊ ማኅበረሰቦች እንዲሁም ተጠቃሚው ሕዝብ ለሕፃናት የሚሰጡ መሰረታዊ አገልግሎት መርሃ-ግብሮች ንድፍና የአስተዳደር ዕቅድ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤

በ/ ለሕፃናት የሚደረግ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አጠባበቅ እንዲስፋፋ ከሕብረተሰቡ የሚገኝ ሀገር በቀል ሀብት በማሰባሰብና ሌሎች የፋይናንስና የቴክኒክ እርዳታ በማድረግ ድጋፍ መስጠት፤

## አንቀጽ 15

## ስለ ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ

1. ማንኛውም ሕፃን ከማናቸውም ዓይነት የኢኮኖሚ ብዝበዛ ሊጠበቅ ይገባል፡፡ አካሉን፣ አእምሮውን፣ ጤናውን፣ ሥነ-ምግባሩን፣ መንፈሱን ወይም ማኅበራዊ እድገቱን ሊጐዳ የሚችል ሥራ ከመሥራት መጠበቅ አለበት፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናትን በሚመለከት መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ሥራን የሚያካትተው ንኡስ አንቀጽ 1 ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ መሆኑን ለማረጋገጥ፤ እንዲሁም የዓለም የሥራ ድርጅት ካወጣቸው ሕጐች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ የሆኑ ሕጐችን ማውጣት እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ በተለይም የሚከተሉትን መፈጸም አለባቸው፡፡

ሀ/ ለማንኛውም ቅጥር ዝቅተኛውን /መነሻውን/ የደመወዝ ልክ በሕግ መወሰን፤

ለ/ የሥራ ሁኔታንና ሰዓትን አግባብነት ባለው ሕግ መወሰን፤

ሐ/ የዚህን አንቀጽ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ተገቢውን የወንጀል ቅጣትና አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች በሕግ መወሰን፤

መ/ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ አደገኛነትን እንዲረዱ በማሰብ መረጃን የማሠራጨት ሥራ ማስፋፋት፤

## አንቀጽ 16

## ሕፃናትን ከጥቃትና ከግርፋት ስለመጠበቅ

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በእንክብካቤ ስም ከሚፈጸም ከማንኛውም ዓይነት ግርፋት፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝ፤ በተለይም በአእምሮአቸውና በአካላቸው ላይ ከሚደርስ ጉዳት፣ ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ ከሚሰነዘርባቸው እንግልትና አግባብነት ከሌለው አያያዝ ለመጠበቅ ሕግ ማውጣት፣ አስተዳደራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ትምህርት ነክ የመሳሰሉ ማናቸውንም ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እርምጃ ለሕፃናቱና ሕፃናቱን ለሚንከባከቡ ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ፣ ልዩ የቁጥጥር ክፍል ማቋቋምንና ሌሎች የመከላከያ መንገዶችን፣ በሕፃናት ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶችና ጉዳቶችም ተለይተው የሚታወቁበት፣ በእነዚሁ ጉዳዮች ላይ ምርመራ እና ሪፖርት የሚደረግበትን እንዲሁም ለሕፃናቱ እንክብካቤ የሚደረግበትን ውጤታማ ሥነ-ሥርዓትን ያጠቃልላል፡፡

## አንቀጽ 17
## የወጣት ጥፋተኞች ፍትሕ አስተዳደር

1. ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተከሰሰ ወይም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሕፃን የሌሎች ሰዎች ሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶች በማክበር ረገድ ያለውን ግንዛቤ በማጠናከርና ለክብሩ ካለው ግንዛቤ ጋር የተጣጣመ እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በተለይ፤
   ሀ/ ማንኛውም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የተደረገ ወይም ተፈርዶበት የታሰረ ወይም በሌላ ሁኔታ ነጻነቱን ያጣ ሕፃን ለግርፋት፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ ለሆነ አያያዝ ወይም ቅጣት አለመጋለጡን የማረጋገጥ፤
   ለ/ ሕፃናት በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት ከጐልማሶች ጋር አለመታሰራቸውን የማረጋገጥ፤
   ሐ/ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተከሰሰ ሕፃን
      I. ጥፋተኛነቱ በተገቢው መንገድ እስኪረጋገጥ ንጹሕ ሆኖ መገመቱን፣
      II. የቀረበባቸው ክስ በቂ በሆነ ዝርዝር በሚገባቸው ቋንቋ ወዲያውኑ እንዲነገራቸው፣ ቋንቋውን ሊረዱት ባልቻሉ ጊዜ ክርክሩ እንዲተረጐም ለመጠየቅ መብት እንዳላቸው፣
      III. መከላከያ መልስ ሲያዘጋጁ ወይም ሲያቀርቡ የሕግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድጋፎች ማግኘታቸውን፣
      IV. ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል ጉዳያቸውን በተቻለ ፍጥነት የማስወሰን፣ ጥፋተኛ በሆኑ ጊዜም ከፍተኛ ደረጃ ላለው የዳኝነት አካል ይግባኝ የማለት መብታቸውን የማረጋገጥ፣

   መ/ መገናኛ ብዙኃን ችሎቱን እንዳይከታተሉ የመከልከል፤
3. ሕፃኑ በፍርድ ሂደት ላይ እያለ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ የሚፈጸሙ አያያዞች ዋንኛ ዓላማ ሕፃኑን የመለወጥ፣ ከቤተሰቡ ጋር

እንዲቀላቀል እና ማኅበራዊ ተሃድሶ እንዲያገኝ የማድረግ ዓላማን የተንተራሰ መሆን አለበት፡፡

4. ሕፃናት በወንጀል ኃላፊነት የማይጠየቁበት ዝቅተኛ ዕድሜ ሊወሰን ይገባል፡፡

## አንቀጽ 18

## ለቤተሰብ የሚደረግ ጥበቃ

1. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ ነው፡፡ የሕብረተሰብ አመሰራረትና እድገት ከመንግሥት ጥበቃና ድጋፍ ያገኛል፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ባልና ሚስት ጋብቻው ጸንቶ ሲኖር ወይም ሲፈርስ ልጆቻቸውን በተመለከተ እኩል መብትና ኃላፊነት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ጋብቻው በሚፈርስበት ጊዜ ለሕፃናት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግ የሚያዙ ድንጋጌዎች መታወጅ አለባቸው፡፡
3. ሕፃናት የወላጆቻቸው የጋብቻ አቋም (ሁኔታ) ተጠቅሶ ቀለብ ከማግኘት ሊከለከሉ አይገባም፡፡

## አንቀጽ 19

## ስለ ወላጅ እንክብካቤ እና ጥበቃ

1. ሕፃናት የወላጅ እንክብካቤና ጥበቃ የማግኘት እንደዚሁም በተቻለ ጊዜ ሁሉ ከወላጆቻቸው ጋር የመኖር መብት አላቸው፡፡ ፍርድ ቤት ለሕፃናቱ የተሻለ ጥቅም ሲል አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ካልወሰነ በቀር ሕፃናት ከፍላጐታቸው ውጪ ከወላጆቻቸው አይለዩም፡፡
2. ከሁለቱ ወይም ከአንዱ ወላጁ የተለየ ሕፃን ከሁለቱም ወላጆቹ ጋር ያለው ዝምድና የመቀጠል ወይም ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት የማድረግ መብት አለው፡፡
3. መለያየቱ የተፈጠረው አንድ ተዋዋይ ሀገር በወሰደው እርምጃ ምክንያት ከሆነ ይኸው ሀገር ለሕፃኑ ወይም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ለሌላው የቤተሰቡ አባል ስለጠፋው የቤተሰብ አባል ወይም አባላት አድራሻ አስፈላጊውን መረጃ መስጠት አለበት፡፡ ተዋዋይ ሀገራት የማፈላለጉ ጥያቄ የሚቀርብለት ሰው ወይም ሰዎች ጥያቄው በመቅረቡ እንዳይጐዳ(ዱ) ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡
4. ሕፃኑ በአንድ ተዋዋይ ሀገር በቁጥጥር ስር እንዲውል የተደረገ ከሆነ በቁጥጥር ስር ያደረገው ሀገር የሕፃኑን መያዝ ለወላጆቹ ወይም ለአሳዳሪዎቹ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ 20

## የወላጅ ኃላፊነቶች

1. ወላጆቹ ወይም ለሕፃኑ ኃላፊ የሆኑ ሰዎች ለሕፃኑ አስተዳደግና ሁለንተናዊ ጉልምስና ቀዳሚ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪ፤

ሀ/ የሕፃኑን ደኅንነት (ጥቅም) በማናቸውም ጊዜ እንደ ዋንኛ ጉዳያቸው የሚያዩ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ/ ችሎታቸውና የገንዘብ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለሕፃናቱ እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማሟላት፤

ሐ/ በሕፃናት ላይ በቤት ውስጥ የሚፈጸሙ ቅጣቶች፣ ከሕፃናቱ ክብር ጋር በተጣጣሙና ሰብአዊ በሆነ ሁኔታ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት፤

ሀ/ ወላጆችን ወይም ለሕፃናት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎችን መርዳት፣ አስፈላጊ ሲሆንም የቁሳቁስ እርዳታ ማድረግ በተለይም ተመጣጣኝ ምግብ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ አልባሳት እና መጠለያን በሚመለከቱ መርሃ-ግብሮች አማካኝነት ድጋፍ ለመስጠት፤

ለ/ ወላጆች ወይም ለሕፃናት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ሕፃኑን ለማሳደግ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ለመስጠት፣ ሕፃናት ተንከባካቢ ተቋማት መመሥረታቸውን ለማረጋገጥ፤

ሐ/ ሠራተኛ ለሆኑ ወላጆች ልጆች እንክብካቤ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 21

## ጎጂ ከሆኑ ማኅበራዊና ባህላዊ ልምዶች መጠበቅ፤

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የሕፃኑን ደኅንነት፣ ክብር፣ ጤናማ እድገትና ጉልምስና ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጎጂ ማኅበራዊና ባህላዊ ልማዶችን ለማስወገድ በተለይም፤

ሀ/ የሕፃኑን ጤና ወይም ሕይወት የሚጎዱ ልማዶችንና ወጎችን፣

ለ/ የሕፃኑን ጾታ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ልዩነት የሚያደርጉ ወግና ልማዶችን ለማስወገድ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡

2. ሴቶችና ወንድ ልጆች የሚፈጽሟቸው ከዕድሜ በታች የሆኑ ጋብቻዎች እና መተጫጨቶች የተከለከሉ ናቸው፡፡ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት እንዲሆንና የጋብቻ ምዝገባ አስገዳጅ እንዲሆን የሚያደርግ ሕግ ማውጣትን ጨምሮ ማናቸውንም እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

## አንቀጽ 22

## ወታደራዊ ግጭቶች

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናትን የሚመለከቱ በወታደራዊ ግጭት ወቅት ተፈጻሚ የሚሆኑ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጎችን ማክበርና መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት በማናቸውም ጥላቻዎች ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በተለይ ሕፃናቱን ለውትድርና ዓላማ ከመመልመል መቆጠብ አለባቸው፡፡
3. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ባለባቸው ግዴታ መሰረት ሲቪሉን ሕዝብ ከወታደራዊ ግጭት የመጠበቅ እንዲሁም በግጭቱ የሚጐዱ ሕፃናት ከግጭቱ መጠበቃቸውንና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ተስማሚ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ ይህ ድንጋጌ በሀገር ውስጥ በተነሳ ግጭት፣ ውጥረትና ብጥብጥ ውስጥ ያሉ ሕፃናትን በተመለከተም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 23

## ስለ ስደተኛ ሕፃናት

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት ጥገኝነት እንዲሰጠው የሚፈልግ ወይም እንደ ጥገኛ የተቆጠረ ሕፃን ከወላጆቹ፣ ከሕጋዊ አሳዳሪው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ሆነም አልሆነም በዚህ ቻርተር፣ በሌሎች ሀገራቱ ተዋዋይ በሆኑባቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና የሰብአዊነት ሕጐች ላይ የተዘረዘሩ ተገቢነት ያላቸውን ጥበቃዎችና ሰብአዊ እርዳታዎችን ማግኘቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ለስደተኛ ሕፃን ጥበቃ ለማድረግ ወይም ድጋፍ ለመስጠት ወይም ወላጆቹን ወይም የቅርብ ዘመዱን ፈለግ ለማግኘትና ከቤተሰቡ እንዲቀላቀል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለስደተኞች ጥበቃ ከሚያደርጉና ድጋፍ ከሚሰጡ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር መተባበር አለባቸው፡፡

3. የሕፃኑን ቤተሰብ፣ ሕጋዊ አሳዳሪ ወይም የቅርብ ዘመድ ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ በዘላቂነት ወይም በጊዜያዊነት በማንኛውም ምክንያት ቤተሰቡን ያጣ ሕፃን የሚሰጠውን ጥበቃ ስደተኛው ሕፃን ያገኛል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በተፈጥሮ አደጋ፣ በሀገር ውስጥ በተካሄደ ወታደራዊ ግጭት፣ አለመረጋጋት ወይም በማናቸውም ምክንያት በተቀሰቀሰ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብጥብጥ የተነሳ ተፈናቃይ በሆነ ሕፃን ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 24

## ጉዲፈቻ

ጉዲፈቻን የሚቀበሉ ተዋዋይ ሀገራት የሕፃኑ ደኅንነት (ጥቅም) ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ሆኖ፤

ሀ/ የጉዲፈቻን ጉዳይ የሚወስኑ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላትን ማቋቋምና ጉዲፈቻው አግባብ ባለው ሕግና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም አግባብነት ባለው አስተማማኝ መረጃ መሰረት መከናወኑንና የሕፃኑ ወላጆች፣ ዘመድ ወይም አሳዳጊዎች አስፈላጊ ሲሆን የሚመለከታቸው ሰዎች የተሰጣቸውን መረጃና ምክር መሰረት በማድረግ ጉዲፈቻውን መቀበላቸውን ማረጋገጥ፤

ለ/ ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብት ሕፃኑ በተወለደበት ሀገር በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ወይም በፎስተር አገልግሎት ወይም በሌላ ማናቸውም ተስማሚ መንገድ ሊያድግ ካልቻለ የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች በተቀበሉ ወይም ባጸደቁ ሀገራት መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ የመጨረሻ አማራጭ መፍትሔ እንደሆነ የመቀበል፤

ሐ/ በሀገራት መካከል በሚፈጸም ጉዲፈቻ የሚሰጥ ሕፃን በሀገር ውስጥ ለሚፈጸም ጉዲፈቻ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችና መመዘኛዎች የተጠበቁለት መሆኑን የማረጋገጥ፤

መ/ በሀገራት መካከል በሚፈጸም ጉዲፈቻ የሕፃኑ ሌላ ሀገር መሄድ ጉዳዩን ለሚያስፈጽሙ የገቢ ማግኛ ዘዴ ወይም መነገጃ እንዳይሆን አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችን የመውሰድ፤

ሠ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሁለትዮሽ ወይም ሌሎች በርካታ ሀገራትን የሚያቅፉ ጉዲፈቻን የሚመለከቱ ስምምነቶችን በማድረግ፤ እንደዚሁም ሕፃኑ በጉዲፈቻ ወደ ሌላ ሀገር ከመሄዱ በፊት ጉዲፈቻው ሥልጣን ባላቸው አካላት ወይም ድርጅቶች መፈቀዱን በማረጋገጥ የዚህን አንቀጽ ዓላማ የማራመድ፤

ረ/ ጉዲፈቻ የተደረገ ሕፃንን ደኅንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን የመዘርጋት ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 25

## ከቤተሰብ ስለመለያየት

1. በማንኛውም ምክንያት ቤተሰቦቹን ለጊዜው ወይም በቋሚነት ያጣ ማንኛውም ሕፃን የተለየ ጥበቃ እና ድጋፍ ማግኘት ይገባዋል፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት፤

   ሀ/ ቤተሰብ አልባ የሆኑ ወይም ለጊዜው ወይም በቋሚነት ቤተሰባቸውን ያጡ ወይም ለእነርሱ የተሻለ ጥቅም ሲባል ከቤተሰባቸው ጋር እንዳይቆዩ የተደረጉ ሕፃናትን የፎስተር አገልግሎትንና ለሕፃናት እንክብካቤ በሚያደርጉ ተስማሚ ተቋማት እንዲገቡ ማድረግን የሚጨምር ተለዋጭ የቤተሰብ እንክብካቤ ማግኘታቸውን የማረጋገጥ፤

   ለ/ ሕፃናቱ ከቤተሰባቸው የተለዩት በወታደራዊ ግጭት ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት በተፈጠረ የሀገር ውስጥ ወይም ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር የተደረገ መፈናቀል ከሆነ ቤተሰባቸውን ለማፈላለግ እና ሕፃናቱን ከቤተሰባቸው ጋር ለማገናኘት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡
3. ሕፃናቱ ተለዋጭ የቤተሰብ እንክብካቤ እንዲያገኙ እና ደኅንነታቸውና ጥቅማቸው በተሻለ ሁኔታ እንዲጠበቅ ለማድረግ እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት የሕፃናቱ አስተዳደግ ቀጣይነት እና የመጡበት ጐሣ፣ ሃይማኖታቸው እና ቋንቋቸው ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

## አንቀጽ 26

## ከአፓርታይድ (የዘር መድልዎ) እና መድልዎ/ልዩነት ስለመጠበቅ፤

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በዘር መድልዎ ሥርዓት ውስጥ ለሚኖሩ እና በዚሁ ሥርዓት ወታደራዊ አለመረጋጋት ስር ባሉ ሀገራት ውስጥ ላሉ ሕፃናት የተለየ ፍላጐት ቅድሚያ በመስጠት በተናጠል እና በጋራ መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡
2. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የዘር፣ የጐሣ ወይም ሌሎች ዓይነቶች ልዩነቶችን/መድልዎችን በሚያራምድ ሥርዓት ወይም ለወታደራዊ አለመረጋጋት

በተጋለጡ ሀገሮች ውስጥ ለሚኖሩ ሕፃናት የተለዩ ፍላጐቶች ቅድሚያ በመስጠት በተናጠል እና በጋራ መሥራት/መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡

3. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በተቻለ መጠን ለእነዚህ ሕፃናት ቁሳዊ ድጋፍ ለማድረግ እና ከአፍሪካ አህጉር ማንኛውንም ዓይነት ልዩነት/መድልዎ እና የዘር መድልዎ ላይ የተመሰረተ ሥርዓትን (አፓርታይድን) ለማጥፋት ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 27

## የወሲብ ብዝበዛ

የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናትን ከማንኛውም ዓይነት የወሲብ ብዝበዛና የወሲብ ጥቃት መጠበቅ አለባቸው፡፡ በተለይም የሚከተሉትን ለመከላከል እርምጃዎች ይወስዳሉ፡፡

ሀ/ ሕፃናትን በማባበል፣ በማስገደድ ወይም በማደፋፈር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግን፤

ለ/ ሕፃናትን በሴተኛ አዳሪነት ወይም ለሌላ የወሲብ ተግባራት መጠቀምን፤

ሐ/ ሕፃናትን ለአስነዋሪ ትርዒቶች፣ ሲኒማዎች እና ፎቶዎች (ፖርኖግራፊ) መጠቀምን፤

## አንቀጽ 28

## አደንዛዥ ዕፅ ስለመጠቀም/ስለማዘዋወር

የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት በአደንዛዥ ዕፆችና በዓለም አቀፍ ሕጐች ሱስ ያስይዛሉ በተባሉ አእምሮ አደንዛዥ ንጥረ ነገሮች እንዳይጠቀሙ፤ እንደዚሁም ሰዎች እነዚህን አደገኛ ዕፆች በማምረት ወይም በማሰራጨት ረገድ በሕፃናት እንዳይጠቀሙ ለመከላከል ማንኛውምን ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 29

## ሕፃናትን ስለመሸጥ፣ በሕፃናት ስለመነገድ እና አስገድዶ ስለመውሰድ

የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት፤

ሀ/ የሕፃናቱን ቤተሰብ ወይም ሕጋዊ አሳዳሪ ጨምሮ በማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ ወይም በማንኛውም መንገድ ሕፃናትን በኃይል አስገድዶ መውሰድን፣ መሸጥን ወይም በሕፃናት መነገድን፣

ለ/ ሕፃናትን ለማንኛውም ዓይነት ልመና መጠቀምን ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 30

## በእስር ላይ ያሉ እናቶች ልጆች

1. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት ለተከሰሱ ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን በመተላለፋቸው ጥፋተኛ ለተባሉ ነፍሰጡር እና ሕፃናት ልጆች ላሏቸው ሴቶች ልዩ እንክብካቤ ማድረግ አለባቸው። ከዚህ አንጻር በተለይም፤

ሀ/ እነዚህን እናቶች አስመልክቶ በሚሰጥ ፍርድ በቅድሚያ እንቅስቃሴያቸው ሳይገደብ (ሳይታሰሩ) የሚፈጸም ፍርድ መጤኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

ለ/ እነዚህን እናቶች ለመንከባከብ በተቋማት ተገድበው በሚቆዩበት እስር ምትክ አማራጭ እርምጃዎችን መውሰድ እና ማበረታታት አለባቸው።

ሐ/ እነዚህ እናቶች የሚቆዩበት አማራጭ ልዩ ተቋማትን ማቋቋም አለባቸው፤

መ/ እናቶች ከሕፃናት ልጆቻቸው ጋር አለመታሰራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤

ሠ/ በእነዚህ እናቶች ላይ የሞት ፍርድ አለመወሰኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

ረ/ የሚፈጸመው እስር ዋንኛ ዓላማ እናቶችን ለማሻሻል፣ ከቤተሰባቸው ጋር ማቀላቀል እና ማኅበራዊ ተሃድሶ መሆን አለበት።

## አንቀጽ 31

## የሕፃናት ግዴታ/ኃላፊነት

ማንኛውም ሕፃን ለቤተሰቡ፣ ለሕብረተሰብ፣ ለመንግሥት እና ለሌሎች በሕግ ዕውቅና ላላቸው ማኅበረሰቦች እና ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ግዴታዎች አሉበት። እድሜያቸው፣ ችሎታቸው እና በዚህ ቻርተር የተቀመጡት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ሕፃናት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፤

ሀ/ ለቤተሰቡ አንድነት የመሥራት፣ ቤተሰቦቹን፣ ታላላቆቹን እና አረጋውያንን ሁልጊዜ ማክበር እና ሲቸገሩም የመርዳት፤

ለ/ አካላዊ እና አእምሮአዊ ችሎታውን ላለበት ማኅበረሰብ አገልግሎት የማበርከት፤

ሐ/ ማኅበራዊ እና ብሔራዊ ትብብርን/አንድነትን የማጠናከር እና የመጠበቅ፤

መ/ ከሌሎች የሕብረተሰብ አባላት ጋር በመቻቻል መንፈስ፣ በመነጋገር እና በመመካከር ላይ በመመስረት በሚያደርገው ግንኙነት የአፍሪካን ባህላዊ ዕሴቶች በማጠናከር እና በመጠበቅ ለሕብረተሰቡ የሞራል ሕልውና አስተዋጽኦ የማድረግ፤

ሠ/ የሀገሩን ነጻነት እና አንድነት የማጠናከር እና የመጠበቅ፤

ረ/ የአፍሪካን አንድነት/ውኅደት ለማራመድ እና ለማሳካት ሁልጊዜ በማንኛውም ደረጃ ችሎታው በፈቀደ መጠን አስተዋጽኦ የማድረግ፤

# ክፍል 2

## ምዕራፍ ሁለት

## የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ኮሚቴ ምስረታ እና አወቃቀር

### አንቀጽ 32

### ኮሚቴ

የሕፃናትን መብቶችና ደኅንነት ለማራመድ እና ለመጠበቅ ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠቀስ የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደኅንነት የባለሙያዎች ኮሚቴ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ ተቋቁሟል፡፡

### አንቀጽ 33

### የኮሚቴው ጥንቅር

1. ኮሚቴው ከፍተኛ ሥነ-ምግባር ያላቸው፣ ሃቀኛ እና የማያዳሉ እንደሁም በሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ጉዳይ በቂ ችሎታ ያላቸው አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት ማንንም ሳይወክሉ በግል ኃላፊነታቸው ያገለግላሉ፡፡
3. ኮሚቴው ከአንድ ሀገር ከአንድ በላይ አባል መያዝ የለበትም፡፡

### አንቀጽ 34

### ምርጫ

ይህ ቻርተር በሥራ ላይ እንደዋለ ወዲያውኑ የመንግሥታት እና የሀገራት መሪዎች ጉባኤ የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት በእጩነት ካቀረቧቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የኮሚቴውን አባላት በምስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ይመርጣሉ፡፡

### አንቀጽ 35

### እጩዎች

እያንዳንዱ የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገር ከሁለት ያልበለጡ እጩዎችን ማቅረብ ይችላል፡፡ እጩዎቹ ከቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የአንዱ ዜግነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንድ ሀገር ሁለት እጩዎችን ካቀረበ አንዱ እጩ የአቅራቢው ሀገር ዜግነት ሊኖረው አይገባም፡፡

## አንቀጽ 36

1. አንድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ቢያንስ ምርጫ ከመካሄዱ ከስድስት ወራት በፊት የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት እጩዎችን እንዲያቀርቡ/እንዲሰይሙ መጋበዝ አለበት፡፡
2. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የእጩዎችን ዝርዝር በፊደል ተራ አዘጋጅቶ ቢያንስ ምርጫው ከመደረጉ ከሁለት ወራት በፊት ለሀገራት እና ለመንግሥታት መሪዎች ያቀርባል/ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 37

## የሥራ ዘመን

1. የኮሚቴው አባላት ለአምስት ዓመታት የሥራ ዘመን ይመረጣሉ፡፡ እንደገና ለመመረጥም አይችሉም፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ምርጫ ከተመረጡት ውስጥ የአራቱ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን የስድስቱ አባላት የሥራ ዘመን ደግሞ አራት ዓመት ይሆናል፡፡
2. የመጀመሪያው ምርጫ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሀገራት እና የመንግሥታት መሪዎች ጉባኤ ሊቀመንበር በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሱትን ሰዎች በዕጣ ይለያል፡፡
3. የኮሚቴው አባላት በተመረጡ በስድስት ወራት ውስጥ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት የሚካሄደውን የኮሚቴውን የመጀመሪያ ስብሰባ ይጠራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በሊቀመንበሩ ይጠራል፡፡

## አንቀጽ 38

## ቢሮ

1. ኮሚቴው የእራሱን የሥነ-ሥርዓት ደንቦች ያወጣል፡፡
2. ኮሚቴው የእራሱን ሹማምንት ለሁለት ዓመታት የሥራ ጊዜ ይመርጣል፡፡
3. ሰባት የኮሚቴ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይኖራል፡፡
4. ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሊቀመንበሩ ያለበት ወገን አቋም የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡
5. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሥራ ቋንቋዎች የኮሚቴው የሥራ ቋንቋዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 39

## ክፍት የሥራ ቦታ

የኮሚቴ አባል ከመደበኛ የሥራ ጊዜ ማለፍ ውጪ ባሉ ማናቸውም ምክንያት ሥራውን ከለቀቀው በእጩነት ያቀረበው አባል ሀገር ከዜጎቹ መካከል በቀሪው ጊዜ የሚያገለግል ሌላ ሰው ይሾማል፡፡ ሆኖም ይህ ተግባራዊ የሚሆነው በጉባኤው ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

## አንቀጽ 40

## ጸሐፊ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለኮሚቴው ጸሐፊ ይሰይማል፡፡

## አንቀጽ 41

## ልዩ መብት

የኮሚቴው አባላት የሥራ ግዴታቸውን በሚወጡበት ወቅት በጠቅላላ ስምምነት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተሰጡ ልዩ መብቶች ይኖሯቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የኮሚቴው ሥልጣን እና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት

## አንቀጽ 42

## ሥልጣን

የኮሚቴው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ በዚህ ቻርተር የተካተቱትን የሕፃናት መብቶች ማራመድ፣ መጠበቅ እና በተለይም፤

I. ሰነዶችን መሰብሰብና በመዝገብ መያዝ፣ በሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ዘርፍ ያሉ አፍሪካዊ ችግሮችን ሁኔታ በሙያዎች ቅንብር ግምገማ እንዲካሄድ ማድረግ፣ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት፣ የሕፃናትን መብቶችና ደኅንነት የሚመለከቱ ብሔራዊ እና አካባቢያዊ ተቋማትን ማበረታታት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለመንግሥታት ያለውን የውሳኔ ሃሣብ መስጠት፣

II. በአፍሪካ የሚኖሩ ሕፃናትን መብቶችና ደኅንነት መጠበቅ ዓላማቸው ያደረጉ መርሆዎችን እና መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤

III. የሕፃናት መብቶችንና ደኅንነትን ማራመድ እና መጠበቅ ከሚመለከታቸው ሌሎች አፍሪካዊ፣ ዓለም አቀፋዊ እና ክልላዊ ተቋማት እና ድርጅቶች ጋር መተባበር፡፡

ለ/ በዚህ ቻርተር የተካተቱትን መብቶች አተገባበር መቆጣጠርና መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ/ በአባል ሀገር፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቋም ወይም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውቅና በተሰጠው ተቋም ወይም ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ የቻርተሩን ድንጋጌዎች መተርጎም፤

መ/ በሀገር እና መንግሥታት መሪዎች ጉባኤ፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ እና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወይም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ማናቸውም አካላት የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን፤

## አንቀጽ 43
## የሪፖርት አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1. ማንኛውም የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገር በዚህ ቻርተር ድንጋጌዎች የተካተቱትን የሕፃናት መብቶች በሚመለከት ስለወሰዷቸው እርምጃዎች እና ስለተገኘው ውጤት በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በኩል ለኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት፤

ሀ/ የመጀመሪያውን ሪፖርት ቻርተሩ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ ያቀርባሉ፡፡

ለ/ ከዚህ በኋላ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን በየሦስት ዓመቱ ያቀርባሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርበው ሪፖርት፤

ሀ/ በሪፖርቱ አቅራቢ ሀገር ስላለው የቻርተሩ አፈጻጸም ኮሚቴው የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው በቂ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

ለ/ በቻርተሩ የተካተቱ ግዴታዎች እንዳይሟሉ ያደረጉ ችግሮች እና የተከሰቱ ሁኔታዎች ካሉ ማመልከት አለበት፡፡

3. የመጀመሪያውን ሪፖርት ሰፋ አድርጎ ለኮሚቴው ያቀረበ አባል ሀገር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2(ሀ) መሰረት ሪፖርት ሲያቀርብ ቀደም ሲል ያስተላለፋቸውን መሰረታዊ መረጃዎች በድጋሚ ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡

## አንቀጽ 44
## አቤቱታዎች ስለመቀበል

1. ኮሚቴው በዚህ ቻርተር የተሸፈኑ ማናቸውንም ጉዳዮች የሚመለከቱ አቤቱታዎችን በአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውቅና ከተሰጠው ማንኛውም ሰው፣ ቡድን ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከአባል ሀገራት ወይም ከተባበሩት መንግሥታት ሊቀበል ይችላል፡፡
2. ማናቸውም ለኮሚቴው የሚቀርቡ አቤቱታዎች የአቅራቢውን ስም እና አድራሻ መያዝ አለባቸው፡፡ አቤቱታዎቹ በሚስጥር ይያዛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

## አንቀጽ 45

## በኮሚቴው የሚደረግ ምርመራ

1. ኮሚቴው ተገቢ ሆኖ ባገኘው መንገድ በዚህ ቻርተር ክልል ውስጥ የሚያርፉ ችግሮችን ለመመርመር፣ ለቻርተሩ አፈጻጸም የሚረዱ ማናቸውንም መረጃዎች ከተዋዋይ ሀገራት ለመጠየቅና ተዋዋይ ሀገራት ቻርተሩን በሥራ ላይ ለማዋል የወሰዷቸውን እርምጃዎች ለመመርመር ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ማናቸውም መንገዶች/ዘዴዎች ለመጠቀም ይችላል፡፡
2. ኮሚቴው ስለሥራው እንቅስቃሴ እና በቻርተሩ አንቀጽ 44 ስር ስለቀረቡ ማናቸውም አቤቱታዎች በየሁለት ዓመቱ ለሀገራትና መንግሥታት መሪዎች ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ሪፖርቱን የሀገራት እና የመንግሥታት መሪዎች ጉባኤ ከተመለከተው በኋላ ኮሚቴው ማሳተም አለበት፡፡
4. የቻርተሩ ተዋዋይ ሀገራት የኮሚቴውን ሪፖርት በየሀገራቸው ለሕዝቦቻቸው በሰፊው እንዲሠራጭ ያደርጋሉ፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 46

### የተነሳሽነት መንፈስ ምንጭ

ኮሚቴው ከሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ሕግ፣ በተለይም ከአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ድንጋጌዎች፣ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር፣ ከሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ፣ ከዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነት እና ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት እና የአፍሪካ ሀገሮች ከተቀበሏቸው ሌሎች ሰነዶች እና ከአፍሪካውያን ዕሴቶች እና ልማዶች የተነሳሽነት መንፈስ ይወስዳሉ፡፡

### አንቀጽ 47

### መፈረም፣ መጽደቅ፣ መቀበል

1. ይህ ቻርተር ለሁሉም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት ፊርማ ክፍት ሆኖ ይቀመጣል፡፡
2. ቻርተሩ ተፈጻሚ የሚሆነው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት ሲጸድቅ ወይም ሲቀበሉት ነው፡፡ የቻርተሩ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነዶች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ጽሕፈት ቤት ይቀመጣሉ፡፡
3. ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተዋዋይ ሀገራት ውስጥ የአሥራ አምስቱን የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከተቀበሉ ከሠላሳ ቀናት በኋላ ይህ ቻርተር የፀና ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 48

### ቻርተሩን ስለማሻሻል እና ስለመከለስ

1. ማንኛውም ተዋዋይ ሀገር ቻርተሩ እንዲሻሻል ወይም እንዲከለስ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ ጥያቄ ካቀረበ ቻርተሩ ሊሻሻል ወይም ሊከለስ ይችላል፡፡ ሆኖም የማሻሻያ ወይም የክለሳ ጥያቄው ሁሉም ተዋዋይ ሀገራት እንዲያጸድቁት ካልተደረገ እና ኮሚቴው በማሻሻያው ላይ ሃሳብ ካልሰጠበት በስተቀር የሀገራት እና የመንግሥታት መሪዎች ጉባኤ እንዲመለከተው አይቀርብለትም፡፡
2. ማሻሻያው በተዋዋይ ሀገራት አብላጫ ድምፅ መጽደቅ አለበት፡፡